**MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION**

**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት**

email: InfoAndPR@moreshwegenie.org

Websites: www.amaramediacenter.org

www.moreshwegenie.org

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *እሑድ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺህ፲፩ዓ.ም.* *ቅጽ ፩ቁጥር ፩*

## በዐማራ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ሊወሰዱ የሚገባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄዎች!

ያለፉ ሁለት ዓመታት ፋሽስት ወያኔና የርዕዮተ ዓለም ወንድሞቹ ለሀያ ሰባት ዓመታት ያህል በመንግሥትነት ተሰይመው ሲሸርቡት የኖሩት መሰሪ ሴራ በተባበረ ሕዝባዊ ተጋድሎ በአስተማማኝ ሁኔታ መበጣጠስ የጀመሩበት ወቅት ቢሆንም ቅሉ ከፋሽስት ወያኔ በኋላ የመጣው አገዛዝ የቆየው አገዛዝ ተቀጥላና ኢትዮጵያ የተዋቀረበትን ርዕዮተ ዓለም የመለወጥ ፍላጎት ስለሌለው ግን የማይተካ መስዕዋትነት የከፈለው ሕዝባችን ዛሬም በነበረው የአፓርታይ ቀንበር ስር ሆኖ መጠኑ በበዛ ጎሰኛነት ፍዳውን እያየ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከተጫነው የአገዛዝ ጭቆና ሁሉ በዐማራው ላይ የወደቀው የአፓርያድ ቀንበር ተቋማዊና መንግሥታዊ ቅርጽ ይዞ የተዘረጋ ሥርዓት በመሆኑ በአይነቱ ይለያል። ይህ ተቋማዊና መንግሥታዊ ቅርጽ ይዞ የተዘረጋው የአፓርታይድ ስርዓት ለሀያ ሰባት ዓመታት ያህል ሙሉ ጊዜውንና አቅሙን አሟጦ በመጠቀም እልቆ ቢስ ጸረ ዐማራ የፈጠራ ታሪኮችንና የፖለቲካ ትርክቶችን ሲያመርትና ሲያሰራጭ በመኖሩ በየትም ዓለም አጀንዳ ሊሆኑ የማይችሉ ጉዳዮች ሁሉ በአገራችን የመናቆሪያ ካርዶችና ሕይዎት የሚያስቀጥፉ ጉዳዮች ሆነዋል። እነዚህ ጸረ ዐማራ የፈጠራ ትርክቶችና የፖለቲካ ድርሰቶች በኢትዮጵያ የፖለቲካ መከራከሪያዎች ሁነው ስላልተመረመሩና ጥፋተኛው አካል ተጠያቂ ስላልተደረገ እነዚህ ስሁት እሳቤዎች ማዕከል ያደረጉት የዐማራው ሕዝብ የሚንቀሳቀስበትን የፖለቲካ ማስቻያ ሜዳ እጅግ ስሱ አድርገውት ይገኛሉ።

ስሱ የሆነውን የዐማራ ፖለቲካ ማስቻያ ሜዳ ስሱነት ያልተገነዘበ ወይንም በተሳሳተው የኢትዮጵያ የግራ ፖለቲካ ትርክት ስሁት ትርጉም የተሰጣቸውን ገና ያልተፍታቱና ጸረ ዐማራ ፍቺ እንዲይዙ ተደርገው የሰረጹ የኮድ ስሞችን ጥቅም ላይ የሚያውል አካል የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ የነዚህ ስሁት ስሞች አሉታዊ ታርጋ ተለጥፎለት በመላው ኢትዮጵያ በስጋት ውስጥ እንዲኖር የተደረገውን ዐማራ ጎልውና የበለጠ አደጋ ላይ ስላለመጣሉ ተጨንቆ ማሰብ አለበት። ይህ ጥንቃቄ በተለይ በዐማራ ስም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ቋሚ መመሪያ መሆን ይኖርበታል።

# በዐማራ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ሊወሰዱ የሚገባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄዎች!

እንደሚታወቀው በፋሽስት ወያኔ የአገዛዝ ዘመን አገርና መንግሥት አልባ እንዲሆን ተደርጎ የዘር ማጥፋት እየተካሄደበት እንዲጠፋ የተፈረደበት መላው የዐማራ ሕዝብ ቢሆንም ከጎልውና አደጋ አኳያ ግን በደቡቡ፣ በደቡብ ምዕራቡና በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል የሚኖረው ዐማራ በሰሜንና መካከለኛው ኢትዮጵያ ከሚኖረው ዐማራ የበለጠ የጎልውና አደጋ አለበት።

ይህን በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚኖረውን ዐማራ ጎልውና ከሌላው አካባቢ ዐማራ አኳያ አደጋ ውስጥ ከጣሉት ምክንያቶች መካከል የተዛባ ፍቺ ተሰጥቷቸው ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት የተሰበኩ የኮድ ስሞች ናቸው።

ካለፉት አርባ ዓመታት ወዲህ ፋሽስት ጣሊያን ጀምሮት ያልተሳካለትን ኢትዮጵያን በጎሳና በመንደር የመከፋፈል አባዜ በመከተል አዲስ የመቶ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ ያቀናበሩ የዐማራ ጠላቶች ረጅሙን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በዐማራ የበላይነት በመፈረጅ በዐማራው ላይ ከፍተኛ የሐጢዓት ክስና የፈጠራ ታሪክ ሲነዙ የቆዩት፤ ዐማራው ሌላውን ኢትዮጵያዊ «በድሏል፤ ጨቁኗል፤ ገዝቷል፤ ወደ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና ምስራቅ የአገራችን ክፍል ለወረራና ለዘረፋ ሂዷል» በማለት የዚዚህ አካባቢ ነዋሪዎችና ዐማራ ያልሆኑ ነገድና ጎሣዎች በጠላትነት ተነስተው እንዲገድሉት፣ ሀብቱን እንዲዘርፉትና እንዲያፈናቅሉት ያደረጉት ዐማራን ትምክተኛ፣ ነፍጠኛ፣ የድሮ ሥርዓት ናፋቂ ወዘተ… የሚሉ ስሁት ፍቺ የሰጧቸው ስያሜዎች ከዐማራው ጋር ተጣብቀውበት ነው።

በሌላ አነጋገር በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ክልልህ አይደለም በተባለው አካባቢ ውስጥ የሚኖረው ዐማራ ከአገሩ አገርህ ሂድ ተብሎ የተባረረውና የዘር ማጥፋት የተካሄደበት ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ፣ ወዘተ በሚል ለተፈጥሩት የኮድ ስሞች ባለእዳ ተደርጎ ነው።

ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ፣ ወዘተ በሚሉ ቅቡል እንዲሆኑ በተደረጉ ስሁት ተግባር የተለጠፈባቸው የኮድ ስሞች ተጨቁነዋል በተባሉ ብሔረሰቦች ዘንድ እንዲታወቅ የተደረገው ዐማራ በፖለቲካ የጠየመው ስሙ ተስተካክሎ የአገርና የመንግሥት፣ የሥርዓትና የሕግ ባለቤት ሳይሆን፤ ደራሽና አዳኝ ወገን ሳይኖረው አዲስ አበባ እየኖሩ በጠላት መሀል ተከቦ የመኖር ድባብ እንዲሰማውና ሕብረተሰባዊ እረፍት እንዲነሳ በተጠና መልኩ ተጣመው የተፈጠሩ የፖለቲካ ቃላቶችን የዐማራ መገለጫ ማድረግ ኃላፊነት የማይሰማው ተግባር ከመሆኑም በላይ በቋፍ ላይ ባለው የዐማራ የጎልውና ቁስል ላይ እንጨት እንደመስደድ ነው።

## በዐማራ  የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ሊወሰዱ የሚገባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄዎች!

ስለዚህ አንድ ለዐማራ የሚቆረቆር ድርጅት ወይንም ግለሰብ በአደባባይ የሚናገራቸው ቃላት ወይንም የሚወስዳቸው አቋሞችን ጥቅምና ጉዳት በመላው ኢትዮጵያ ተበታትኖ ኅልውናው ቋፍ ላይ እንዲሆን ተደርጎ በሚኖረው ዐማራ ላይ ከሚያስከትሉትን አሉታዊ ውጤቶች አኳያ መመዘን ይኖርበታል።

በአደባባይ የሚያስተጋባቸውን ንግግሮች ወይንም በይፋ የሚወስዳቸውን አቋሞች ከግለሰባዊ ግትርነትና ከአፈር አይመልሰኝ ጨዋታ ተላቆ የአደባባይ ንግግሮቹንና ይፋዊ አቋሞቹን ደግሞ ደጋግሞ በማጤን ፋይዳቸውን በጠላት ተከቦ እንደሚኖር እንዲሰማው ከተደረገው ዐማራ ኅልውና አኳያ መመዘን የማይችል የዐማራ ድርጅት ቢኖር የዐማራን ሕዝብ ትግል ዳር ለማድረስ ተስፋ የማይጣልበት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል።

ስለሆነም፣ ሁሉም የዐማራ ድርጅቶች የቋንቋ አጠቃቀማቸውን እንዲመዝኑና የዐማራውን ስነልቦናና አመለካከቱን የሚያንጸባርቁ ይሆን ዘንድ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት በአንክሮ ይጠይቃል።

**ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!**

**ትግላችን ትውልዳዊ ነው፤ የዐማራው መደራጀት የኅልውናውና የማንነቱ መሠረት ነው!**

**ኢትዮጵያ በጀግኖች እና ቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ፀንታ ትኖራለች!**